# ምስጢረ ሥላሴ (ነገረ ሥላሴ)

«መቅድመ ኵሉ ንስብክ ሥላሴ ዕሩየ ወቅዱስ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ከሁሉ አስቀድመን በአካል ልዩ በቅድስና (በክብር) አንድ የሆነውን ሦስትነት እንስብካለን። ይኸውም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው» ሲል ጎርጎርስ ነባቤ መለኮት (ቴኦሎጎስ) አስተምሮአል (ሃያማኖተ አበው፣ጎርጎርዮስ፣ ገጽ ፪፻፲)።

የምስጢረ ሥላሴ መሠረቱና ምንጩ ቅዱስ መጽሐፍ ነው። የምስጢረ ሥላሴ ትምህርት በሚገባ ጐልቶ የተገለጸው፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለመለወጥ ፍጹም ሰው ከሆነ ወዲህ ነው።

## <u>ጥያቄ፡-</u>ምስጢረ ሥላሴ ማለት ምን ማለት ነው?

በመለኮት፣ በባህርይ (በህላዌ)፣ በፈቃድና በሥልጣን አንድ የሆነው እግዚአብሔር፣ የአካል፣ የገጽ፣ የስምና የግብር ሦስትነት እንዳለው የምናምነው እምነት ምስጢር ሥላሴ ይባላል።

## <u>ጥያቄ፡-</u>እግዚአብሔር የአካል ሦስትነት አለው ስንል ምን ማለታችን ነው?

በመለኮት አንድ የሆነው እግዚአብሔር፣ የአካል ሦስትነት አለው ማለት፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይባላል ማለት ነው። በሌላም አነጋገር፣ ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ ለወልድም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ፣ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ እንዳለው የምናምነው እምነት ምስጢረ ሥላሴ ይባላል። የሦስቱም (የሥላሴም) የስም ሦስትነት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው።የግብር ሦስትነታቸውም አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ ነው። ይኸውም፣ ወላዲነት፣ ተወላዲነት፣ ሠራፂነት ማለት ነው።

## <u>ጥያቄ</u>፡-እግዚአብሔር አብ ለምን አባት (አብ) ተባለ?

እግዚአብሔር አብ ወልድን ከባሕርዩ (ከህላዌው) እምቅድመ ዓለም ስለ ወለደው አብ (አባት) ተባለ። ወልድም ከአብ ባሕርይ ስለ ተወለደ (ስለ ተገኘ) የአብ ልጅ ተባለ። ስለዚህ አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ ይባላሉ። ስለዚህም ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ «ከጥንቱ ከዘላለም ጀምሮ ተሾምኩ፤ ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ፣ ቀላያት ገና ሳይፈጠሩ እኔ ተወለድኩ፤ ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፣ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድኩ» (ምሳ.፰፥፳፫-፳፭)። እራሱ እግዚአብሔር አብም፣ «በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው» ሲል መስክሮለታል (ማቴ.፫፥፲፯)። በተጨማሪም፣ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት» ሲል አረጋግጦአል (ማቴ.፲፯፥፭) መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስም፣ «እኔም አይቻዋለሁ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ እመስክራለሁ» ብሎአል (ዮሐ.፩፥፴፬)። ቅዱሳን አባቶቻችን ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንትም በቀኖናቸው፣ «ሁሉን በፈጠረ፣ ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፣ አንድ አምላክ በሚሆን በእግአብሔር አብ እናምናለን፤ እምቅድመ ዓለም ከአብ በተወለደው፣ ከዓለም በፊት ከአብ ጋር ህልው ሆኖ በኖረው፣ የአብ አንድ ልጅ በሆነው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን» ብለዋል (ጸሎተ ሃይማኖት)።

## <u>ጥያቄ</u>፦እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አካልና ፍጹም ገጽ ያለው መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው (የወጣው) ከአብ ብቻ ነውን?

አዎን፤ ወልድ ከአብ ብቻ እንደ ተወለደ፣ መንፈስ ቅዱስም እንዲዚሁ የሠረፀው ከአብ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረፀ መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ እንዲህ ብሎአል፤ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) እርሱ ከአብ የሚወጣ (የሚሠርፅ) የእውነት መንፈስ በመጣ ግዜ እርሱ ስለ እኔ ይመስክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ አንስቶ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመስክራላችሁ» (ዮሐ.፲፭፥፳፮-፳፯)።

መቶ አምሳው ቅዱሳን አበውም፣ ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ቅዱሳን አበው ያስተማሩትን ተከትለው፣ «ጌታና ማሕየዊ በሆነው፣ ከአብ በሠረፀው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ ከአብና ከወልድም ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመስግነዋለንም» ብለዋል (ጸሎተ ሃይማኖት)። ቅዱስ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያም፣ «መንፈስ ቅዱስን እናውቀዋለን (እናምነዋለን)፤ መንፍስ ቅዱስ እንደ አብ፣እንደ ወልድ፣ እንደ ባሕርያቸው ገናንነት በገጹ፣ በአካሉ፣ በመልኩ ያለ ፍጹም የባሕርያ አምላክ እንደሆነ እናምናለን» ሲል አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፹፩)። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ባሕርይ (ከአብ ህላዌ) ስለ ሠረፀ እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አምላክ ነው፤ በዚሁ መሠረት አብ ፍጹም አምላክ፣ ወልድ ፍጹም አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ስለሆነ፣ በመለኮትና በባሕርይ አንድ ስለሆኑ፣ ሦስቱም ሦስት አማልክት፣ ሦስት አጋእዝት አይባሉም፤ ሦስቱም አካላት አንድ አምላክ፣ አንድ እግዚአብሔር አንድ ፈጣሪ ይባላሉ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም። ሐዋርያዊ እየተባለ የሚጠራው ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ስለዚሁ ሲጽፍ፣ «አብ አምላክ ነው፤ ወልድም አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው፤ ነገር ግን ሦስት አማልክት አይባሉም፤ አንድ አምላክ ነው እንጂ» ሲል አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፸፬ ቁ.፬)።

## <u>ጥያቄ</u>፦አብ አምላክ ከሆነ፣ ወልድም አምላክ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ከሆነ ሦስቱም ሁሉ እንዴት አምላክ አይባሉም? (እንዴት ሦስት አምላክ አይባሉም?)

ሦስት አማልክት አይባሉም፤ ምክንያቱም የሦስቱ ባሕርይ (ህላዌ)፣ የሦስቱም አካለት መለኮት (አምላክነት) አንድ ብቻ ነውና። በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር በአካል ሦስት ስለሆነ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላል፤ በመለኮት ግን አንድ ብቻ ስለሆነ አንድ አምላክ፣ አንድ ፈጣሪ፣ አንድ እግዚአብሔር ይባላል።

## <u>ጥያቄ</u>፦እግዚአብሔር በአካል፣ በገጽ ሦስት፣ በመለኮት አንድ መሆኑን የሚያመለክት ምሳሌ ይገኛልን?

አዎን፤ የቤተክርስቲያን መምህራን ያስተማሩባቸው ብዙ ምሳሌዎች አሉ፤ ከእነርሱም ጥቂቶቹ የሚቀጥሉት ናቸው፦

፩. ሰው

ሰው በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ይመደባል። ይኸውም፣ ሀ/ልብ፣ ለ/ቃል፣ ሐ/እስትንፋስ ናቸው። እንደ ልብ አብ፣ እንደ ቃል ወልድ፣ እንደ እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ። በዚሁ መሠረት፣ አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ይባላሉ።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይህን ምሳሌ በመውሰድ ሦስት ኩነታት ብለው ሰይመውታል። ይኸውም ከዊነ ልብ፣ ከዊነ ቃል፣ ከዊነ እስትንፋስ ማለት ነው። በተጠቀሰው ምሳሌ መሠረት የሰው ልብ ምንጊዜም ኩነቱን (ለባዊነቱን) ሳይለቅ በራሱ ከዊን ጸንቶ ማለት ከዊንነቱን ሳይተው፣ ቃልና እስትንፋስ ያስገኛል፤ ቃል

ም ቃልነቱም ሳይተው፣ በራሱ ከዊንነተ በመጽናት ልብና እስትንፍስ ይናገሩታል፤ እስትንፋስም በራሱ ከዊን ነት በመጽናት የልብና የቃል እስትንፋስ ነው።

በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር አብም በራሱ አካልና በራሱ ገጽ፣ በራሱ ከዊን በመጽናት፣ ለወልድ ና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ማለት መገኛቸው ነው። ወልድም ቃል ነውና በራሱ አካልና በራሱ ገጽ፣ በራ ሱ ከዊን ማለት በራሱ ቃልነት በመጽናት፣ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነውና ይናገሩበታል። መንፈስ ቅዱስም በራሱ አካልና በራሱ ገጽ፣ በራሱ ከዊን በመጽናት፣ ለአብና ለወልድ (ለቃል) እስትንፋሳቸው (ሕ ይወታቸው) ነው።

ይህን የከዊን ሐተታ አስመልክቶ ከ፫፻፴፯-፫፻፺፪ ዓ.ም ድረስ የሮም ሊቀ ጳጳስ የነበረው አቡሊ ዲስ (ዩልዩስ) ቀጥሎ ያለውን ጽፎአል፤ «አብኒ ልቡናሆሙ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ሕይወቶሙ ለአብ ወለወልድ፤ አብም የወልድና የመንፈስ ቅ ዱስ ልባቸው ነው፤ ወልድምለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ እስ ትንፋሳቸው ነው» (ሃይማኖተ አበው፣አቡሊዲስ ኀበ. በርደጊስ ፍ.፪፣ገጽ ፻፴፰)።

ቅዱስ ዳዊትም፤ «ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልአ ምድረ፣ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት፣ወ እምእስትንፋስ አፍሁ ኵሉ ኃይሎሙ» ብሎአል። ማለት «ሣህሉ ለእግዚአብሔር» ባለው እግዚአብሔር አብን፣ «ወበቃለ እግዚአብሔር» ባለው እግዚአብሔር ቃልን (ወልድን)፣ «ወእምእስትንፋስ አፉሁ» ባለ ው እግዚአብሔር መንፈስቅዱስን አመልክቶአል (መዝ.፴፪(፴፫)፥፮-፰)። የቤተክርስቲያን ሊቃውንትም በ ሙሉ በቅዱስ ዳዊት አገላለጽ ተስማምተውበታል።

**፪. ፀሐይ**

ሁላችን በየቀኑ ወደ ሰማይ ቀና እያልን የምንመለከታት ፀሐይ ሦስት ነገሮች አሉዋት፤ ይኸውም ፦ ሀ/ዐውድ ወይም ክበብ ለ/ብርሃን ሐ/ሙቀት ናቸው። በዚሁ መሠረት በክበቧ እግዚአብሔር አብ፣ በብ ርሃንዋ እግዚአብሔር ወልድ፣ በሙቀቷ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፤ ነገር ግን ፀሐይ ሦስት ነገሮች ስላሏት አንድ ፀሐይእንጂ ሦስት ፀሐይ እንደማትባል ሁሉ፣ እግዚአብሔር የአካል ሦስትነት ስላለ ው አንድ አምላክ አንድ ፈጣሪ ነው። በአምላክነቱ ሁለትነት ወይም ሦስትነት የለውም። ዘላለም አንድ ብቻ ነው። «አብ ፀሐይ ነው፤ ወልድም ፀሐይነው፤ መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ።ነገር ግን ከሁሉ በላይ ያለው የእውነት ፀሐይ እግዚአብሔር አምላክ አንድ ነው» ሲል አባ ሕርያቆስ መስክ-
ሮአል (ቅዳሴ ማርያም፣ ቁ.፸፫)።

**፫. እሳት**

እሳት ባሕርዩ (ህልዌው) አንድ ነው፤ ነገር ግን ሦስት ነገሮች አሉት፤ ያኸውም፦ ሀ. አካሉ ወይም ፍህሙ ለ. ብርሃኑ ሀ. ሙቀቱ ናቸው። በዚሁ መሠረት እንደ ፍሕመ አብ ይመስላል፤ እንደ ብርሃኑ ወል ድ ይመስላል፤ እንዳ ሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል። እሳት ሦስት ነገር ስላለው አንድ እሳት እንጂ ሦ ስት እሳት አይባልም፤ ምክንያቱም በባህርዩ አንድ ብቻ ነውና። እግዚአብሔር የአካል ሦስትነት ስላለው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ቢባልም፣ ባህርዩም ወይም መለኮቱ አንድ ስለሆነ፣ ሁል ግዜ አንድ እግዚአብ ሔር አንድ አምላክ እንደሆነ ሲመስግንና ሲቀደስ ለዘላለም ይኖራል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ አበው አድሮ፣ «አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ፀሐይና ብርሃን ዋዕይም ነን። አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም እሳትና ነበልባል ፍሕምም ነን» ብሎአል (ቅዳሴ ዘሰለስቱ ምዕት፣ ቁ.፵፮-፵፰)።

ሰለዚህ እንደ ፀሐይና እንደ እሳት እግዚአብሔር በአካል ሦስት ሲሆን፣ በባሕርይ አንድ ነን። በዚሁ መሠ ረት አንድ አምላክ አንድ ፈጣሪ እንደሆነ ዘላለም ይኖራል።

## <u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር አብ ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ወልድን ወለደው ማለት ወይም እግዚአብሔር ወልድ እምቅድመ ዓለም ከእግዚአብሔር ተወለደ ማለት ምን ማለት ነው?

እምቅድመ ዓለም (ከዓለም በፊት) እግዚአብሔር አብ ወልድን ወለደው ማለት፣ ወይም ዓለም ከ መፍጠሩ በፊት እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ ማለት ሰው ከሰው እንደሚወ ለደው ዓይነት ተወለደ ማለት አይደለም። ወይም አብርሃም ይስሐቅን ወለደው እንደምንል፣ እግ

ዚአብሔር አብም ወልድን ወለድው ማለታችን አይደለም። እግዚአብሔር ፍጹም ረቂቅ መንፈስ ነውና በዚህ ዓይነት ሊታሰብ አይገባም። ነገር ግን ብርሃን ከብርሃን እንደሚገኝ፣ ወይም የፀሐይ ብርሃን ከዐውደ ፀሐይ ማለት ከክበበ ፀሐይ እንደሚገኝ፣ እግዚአብሔር ወልድም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ፍጹም ብርሃን ከሆነው እግዚአብሔር አብ ስለተገኘ ተወለደ ይባላል። ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ አበው የወልድን ከአብ ባህርይ መገኘት አስመልክተው፣ «ከባህርይ አምላክ የተገኘ የባሕርይ አምላክ፣ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፣ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ» ሲሉ አስተምረዋል (ሃይማኖተ አበው፣ ምዕ.፲፰፥ ቁ.፲፯ ገጽ፶)።

ቅዱስ አትናቴዮስ ዘእስክንድርያም፣ «ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፣ አምላከ ጽድቅ ዘእምአምላከ ጽድቅ፣ ብርሃን ዘእምብርሃን ዘበአማን፣ ማሕየዊ ዘእማሕየዊ፤ ከባህርይ የተገኘ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ፣ ከእውነተኛ ብርሃን የተገኘ እውነተኛ ብርሃን፣ አዳኝ ከሆነ አብ የተገኘ እውነተኛ መድኅን በሚሆን ተቀዳሚና የተታይ በሌለው በአንድ በእግዚአብሔር ወልድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን» ሲል አስተምሮአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፹፬)።

ቅዱስ ዲዮናስዮስ ዘአርዮስፋጎስም ስለዚሁ ሲያስረዳ፣ «አብ ብርሃን ነው፤ ከአብ የተወለደ ቃሉ ወልድምከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፤ ከአብ የሠረፀው መንፈስ ቅዱስም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፤ ከአብ የወልድ መወለድ፣ የመንፈስ ቅዱስ መሥረፅ እጅግ ይደነቃል እንጂ አይነገርም (ሊነገር አይቻልም) ብሎአል(ሃይማኖተ አበው፣ ምእ.፲ ቁ.፲፱ ገጽ.፴፭)።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ብርሃን ነው ከተባለ ወልድ ከአብ በኋላ የተገኘ አያስኝም ወይ?**

እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ በመገኘቱ ተወለደ ቢባልም፣ በፊት ያልነበረ ሆኖ በኋላ ተገኘ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮትና ባሕርይ አንድ በመሆን ቃለ አብ፣ ወልዱ ለአብ እየተባለ የነበረና ያለ ነውና ከአብ በኋላ የተገኘ አያስኘውም። ይህን ታላቅ ምስጢር አስመልክቶ የአንካራው ሊቀ ጳጳስ ቴዎዶጦስ እንዲህ ሲልአስተምሮአል፤ «ወልድ ዋሕድ ብርሃን ይባላል፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፣ ከብርሃን በኋላ የተገኘ ነው አይባልምና፤ ያ ብርሃን በተገኘ ግዜ እርሱ ከተገኘበት ብርሃን ጋር አንድ ሆኖ ዘወትር ይኖራል እንጂ፤ ብርሃን ዓለም ሁሉ ሳይፈጠር ሁል ግዜ ከአብ ጋር ህልው የሚሆን የወልድን ነገር ያስረዳል» (ሃይማኖተ አበው፣ ምዕ.፶፫ ቁ.፲ ገጽ.፻፷፫)።

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ማለት ሦስቱ አካላት በዘመንም ሆነ በዕለት እንደማይቀዳደሙ፣ ሦስት መቶአሥራ ስምንቱ አበው ሲመሰክሩ እንዲህ ብለዋል፤ «አብ ከወልድ ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም፤ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም፣ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም፣ ሥሉስ ቅዱስ በዘመኑ፣ በቀኑ ሁሉ በግብርም፣ በስምም ሳይለወጥ፣ ሳይፋለስ ጸንቶ ያለ ነውእንጂ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፶፩)።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር በአካል፣ በስምና በገጽ ሦስት ከሆነ በመለኮትም ሦስት ነው ማለት ይቻላልን?**

አይቻልም፤ እግዚአብሔር ሦስት አካለት እንዳሉት ሦስት መለኮት የለውምና፤ የሦስቱ አካላት መለኮት ሁል ግዜ አንድ ብቻ በመሆኑ፣ ሦስቱም አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ፣ አንድ ፈጣሪእንደሆኑ ለዘላለም ይኖራሉ። የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ ብቻ መሆኑ በርከት ያሉ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አስተምረዋል። ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ መለኮት አንድ መሆኑን ሲመሰክር፣ «ወልድ የአብ ቀኝ እጅ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ምክሩ ነው፤ የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ ቅዱሳት መጽሕፍት ያስረዳሉ፤ መለኮት የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አንድነታቸው (አዋሐጃቸው) ነው የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ በዚህ አውቀን» ሲል አስረድታል (ሃይማኖተ አበው፣ ምዕ.፳፭፥ ገጽ.፷፬)። ቀጥሎም ይህ ቅዱስ መምህር እንዲህ ይላል፤ «ነገር ግን መለኮት አንድ መሆኑን በሚገባ እንወቅ፤ በሦስቱ አካላት እ

ንመን፤ የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ መሆኑን ፈጽመን አንካድ» (ሃይማኖተ አበው፣ ምዕ.፴፮፥ ገጽ.፸፮)።

ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ እንዲህ ይላል፤ «የሦስቱ አካላት መለኮት ፍጽም አንድነት (ፈጽሞ አን ድ መሆኑን) ልናውቅ ይገባናል፤ የእርሱ የሚሆነውን መለኮት አንድ በማድረግ እናዋህድ፤ በአብ ወላዲነት አሠራፂነት መለኮት አንድ ነው በምትል ሃይማኖት እንመን፤ ወልድ ከአብ ተወልዶአል ና፤ መንፍስ ቅዱስም ከአብተገኝቶአልና፤ አብ ከወልድ፣ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም፣ ወ ልድ ከአብ በመወለዱ መንፈስ ቅዱሰም ከአብ በመሥረፁ የፈጣሪያችን የሦስትነት መለኮት አንድ ይሆናል» (ሃይማኖተ አበው፣ ምእ.፵፬፥ ገጽ.፻፺)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት መናፍቃንን ለመገሠጽና መለኮት አንድ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲ ህ ሲል ጽፎአል፤ «ከእውቀት ከሃይማኖት የተለዮ መናፍቃን ከቅድስት ሥላሴ መለኮት መክፈልን በአካላት መቃለልን ሊያመጡ አይድፈሩ፤ ሶስት አማልክት ብለን አንስግድም፤ አንድ አምላክ ብለን እንስግዳለን እንጂ፤ በስም ሦስት ናቸው እንላለን፤ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ ባ ሕርይ (አንድ ህላዌ) አንድ መለኮት ናቸው፤ በአንድ መለኮት፣ በአንድ ባሕርይ (በአንድ ህላዌ) የ ጸኑ ሦስት አካላት ሲሆኑ፣ ከሦስቱ አንዱ የሚበልጥ፣ አንዱ የሚያንስ አይደለም፤ በማይመረመር በአንድ ክብር የተካከሉ ናቸው እንጂ» (ሃይማኖተ አበው፣ ምእ.ል ቁ.፬፻፲፬)።

ቅዱስ ቄዎርሎስ ዘእንክንድርያ፣ «አንድ መለኮት፣ አንድ ህላዌ (አንድ ባሕርይ)፣ አንድ ኃይል፣ አንድ ልዕልና፣ አንድ ጌትነት፣ አንድ ክብር፣ ከጥንት አስቀድሞ የነበረ አንድ ቀዳማዊነት ነው፤ በሦስት አካላት፣ በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው፤ ግዙፋን አይደሉም ያልተፈጠሩ ናቸው፤ ድካም የማይስማቸው የማይለወጡናቸው፤ ለዘመናቸውም ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውም» ሲል አስረድቷ ል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ. ፬፻፶፮)።

አባ ዲዮናስዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘአንጾኪያም፣ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን መለኮት አስመልክቶ ሲያስረዳ፣ «ወሶበሂ ንሬሲ ቅድስተ ስላሴ ፍሉጣነ መለኮት ዘከመ እላቲሆሙ፣ ንትአመን እምነተ ስይጣናዌ፤ ቅድስተ ሥላሴን እንደ አካላታቸው የተለየ መለኮት (ሦስት መለኮት) አላቸው ብለን የምናምን ከሆነ፣ እምነታችን ስይጣናዊ ነው» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፭፻፴፬ ቁ.፫)። ስ ለሆነም በአካልና በገጽ ሦስት፣ በመለኮትና በባሕርይ አንድ በሆነው አምላካችን፣ መላውን የሰው ልጅ ከሞተ ኃጢአት ያድን ዘንድ ብሑተልደት (አንድያ) ልጁን ወደ ዓለም ልኮ እርሱም መላ የሰውን ልጅ አዳነ።

ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶሳዊት በአቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ 1991